# አማራነት ፈተና የሆነበት አርቲስት ፋሲል ደመወዝ (ከጎንደር እስከ ሲያትል)!

July 7, 2017

በአሜሪካ የESFNA – Seattle የስፖርት አዘጋጆች ታዋቂውን አርቲስት ፋሲል ደመወዝን የስፖርት ዝግጅቱ እየተካሄደበት ባለው ስታዲዮም እንዳይገባ እገዳ እንደጣሉበት ታወቀ። ምክንያት?
በአማራነቱ  እና በወገኑ የማይደራደር ኩሩ ዜጋ በመሆኑ!!




ታዋቂው አርቲስት ፋሲል ደመወዝ እንከን የማይወጥለት የአማራ ብሎም የሃገሪቱ የባህል አምባሳደር ነው። በባህላዊ ሙዚቃዎቹ ሁላችንንም አስጨፍሯል፤ አዝናንቷል፤ አስለቅሷል፤ አስፎክሯል፤ በትካዜ ማእበልም እንድንሰጥም አድርጎናል። ፋሲል በባህሪው የዋህ ፤ ገራገር ፤ ቀና ፤ ተጫዋች ፤ ላመነበት ነገር ወደ ኋላ የማይል እንዲሁም በአማራነቱ የማይደራደር እንቁ አርቲስታችን ነው። ለስደት ከመብቃቱ በፊት ሃገር ቤት እያለ የወልቃይት እና የመተማ መሬቶች በትግራይ እና ሱዳን ሽፍቶች በመወሰዳቸው ቁጭት ውስጥ ገብቶ ‘አለ ነገር’ በሚል ርዕስ የሰራውን ዘመን ተሻጋሪ እና ልዩ ሙዚቃ ዛሬም ከህሊናችን እና አንደበታችን አይጠፋም።

በዚያ ድንቅ ስራው
“አለ ነገር አለ ነገር፤
ጎንደር እና ጎጃም መሬም አለ ነገር፤
መሃል ሸዋም አለ ነገር ዘንድሮ አለ ነገር ፤
መቼም ታመን ታመን አንገንት ደፍተን አንቀር።”

እያለ ብሶታችን እና አማራዊ በደላችንን በሚያምር የኪነጥበብ ትሩፋት ያስተጋባ ትልቅ ባለውለታችን ነው ፋሲል። የዚህ ግጥም ደራሲ ራሱ ፋሲል ሲሆን ሙዚቃው እስከዛሬም ድረስ እያደረ እንደ ወይን

የሚጣፍጥ ተወዳጅ ስራ ነው። በዚህ ሙዚቃው የተነሳ የደረሰበት መከራ ተዘርዝሮ አያልቅም። ህዋሃት አድኖ ከያዘው በኋላ በአማራነቱ እና የወገኖቹ ድምጽ ስለሆነ ብቻ አስሮ ፤ ገርፎ እና አሰቃይቶ ለስደት ዳረገው። ተወዳጁ አርቲስትም ቅስሙ ተሰብሮ የሚወዳት ሃገሩን እና ህዝቡን ጥሎ ወደ ሃገረ አሜሪካ አቀና።

ፋሲል ወደ አሜሪካ ከተሰደደ በኋላም ቢሆን የወገኖቹን ህመም የሚረሳ አንጀት የለውም እና የሙዚቃ ስራዎቹን ከመስራት ወደ ኋላ አላለም። 'እንቆቅልሽ' የሚለው ዜማ ስለ ሃገር አንድነት እና የሉአላዊነት ክብር የሰበከበት ቆንጆ ስራው ነበር። ሃገሬን አሳልፌ አልሰጥም የሚል እድምታ ያለው ይህ ሙዚቃ በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅ ስራ እንደሆነ ሊዘልቅ ችሏል። ከምንም በላይ ግን አምና በአማራ ተጋድሎ ወቅት የአማራ ህዝብ ለነጻነቱ ሆ ብሎ ሲነሳ ፋሲልም እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። 'የአማራይቱ ልጅ' በሚል ድንቅ ዜማ ብሶታችንን እና የትግላችንን አላማ አስተጋባ እንጂ

"አማራነት እምነት ፤ አማራነት ማተብ፤
ለወገን መታመን ከራስ በላይ ማሰብ"

እያለ የአማራን ድንቅ ስነ-ሰባዊ ባህሪይ ካስተጋባ በኋላ

"የአማራይቱ ልጅ ሆ በል እያለ
በዱር ገደሉ ሲማማል ዋለ።
ደግሞ ደግሞ ደግሞ ባይኔ፤
አትንኩኝ ሲል አየሁ ጀግናው ወገኔ"

እያለ ለዚህ ድንቅ እና ጀግና ህዝብ አዚሞለታል።

የአማራ ተጋድሎ በቀጠለበት ወቅት የአማራ የፖለቲካ ድርጅቶች ስለ አማራ መደራጀት እና ታጋይ ህዝቡን ለመርዳት ባዘጋጁቸው የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ላይም ያለምንም ማንገራገር እየተገኘ ለሚወደው ህዝብ ውለታ መዋሉን አላቆመም።

ይሁን እንጂ በአማራነቱ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አይናቸው ደም የለበሱ የአንድነት ሃይሉ የፖለቲካ ቆሞቀሮች ፋሲልን በክፉ አይን ማየት የጀመሩት ገና ድሮ ነው። በአማራ ፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የኪነጥበብ ስራዎችን እንዳያቀርብ ከማስጠንቀቅ ባለፈ አሉባልታም ሲነዙበት ከርመዋል። አሁን ደግሞ ጭራሽ ይባስ ብለው በሲያትል እየተካሄደ ባለው "የኢትዮጵያዊያን የስፖርት እና ባህል ፌስቲቫል" ላይ 'ለምን አማራ ብለህ ዘፈንክ' በሚል በዝግጅቱ ስራውን እንዳያቀርብ እንዳገዱት እሱ ራሱ በአንደበቱ ተናግሯል።

ኢትዮጵያዊነትን ጠፍጥፎ የሰራው የአማራ አብራክ በ'ኢትዮጵያዊያን ባህል' ላይ ታገደ ሲባል መቸም የማይገረም የለም። ፋሲልም በአማራነቱ ሌላ ዙር በደልን ከሀገር ቤቱ የአምባገነን መንግስት ሳይሆን ከውጭ ሃገሩ አምባገነን ዳግማዊ ወያኔ (አንድነት ሃይሉ) ለመቀበል ተገዷል። ይህንንስ ለማን አቤት ይባል ይሆን?

እንደ ጃኪ ጎሲ አይነት ኮስሞቲክስ አርቲስቶች በሚፈነጩበት ሜዳ የማእከላዊ ስቃይን የተቀበለው አርቲስት ፋሲል ደመወዝ ስታዲየም ድርሽ እንዳይል አድማ ሲመታበት እንደማየት ምን ደም የሚያፈላ ነገር አለ? ይህ የባህል ፌስቲቫል እንደ ሌሎቹ የአንድነት ማህበራት እና ሃይሎች መፈራረስ እና መበተን ካልፈለገ

ጸረ-አማራነቱን ሊያቆም ይገባል። ፋሲልንም ይቅርታ እና ካሳ ከፍሎ በዝግጅቱ ሊያሳትፈው ይገባል። ያለበለዚያ በዚህ የባህል ፌስቲቫል ላይ አማራዎች ባይኮት በማድረግ ቀስ በቀስ ራሳቸውን ቢያገሉ ተጠያቂው ራሱ የስፖርት ፌደሬሽኑ ነው!

ጨው ሆይ ለራስህ ስትል ጣፍጥ
አለበለዚያ አሞሌ ነው ተብለህ ትወረወራለህ!

CC –
ESFNA – Seattle
#ዮሃንስ – #ከቤተ #አማራ